# ማሳሰቢያ

1 .  እግ\ር ሲያትል ከተማን አሳልፎ እንዲሰጠን አጥብቀን እንጸልይ;;

2 . ስለ ኢትዮጵያ ምድርና ስለ ኤርትራ ሁል ግዜ በእግ\ር ፊት እንጸልይ ።

3 . በአለም ዙርያ ስለምያገለግሉ የእግ\ር ባሪያዎች በመከራ ምክንያት ወንጌልን ከመስበክ ፎቀቅ እንዳይሉ በጸሎት እንድንደግፋቸው ያስፍፈልጋል;;

4 . በበሽታ ስለሚሰቃዩ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ስቃያቸውን እንደ ስቃያችን

መከራቸውን እንደመከራችን ወስደን ተሰምቶን በእግ\ር ፊት ዘወትር እንጸልይላቸው ።

5 . በቅድስናና በጽድቅ በንጽህና እንዳንመላለስና እግ\ርን እንዳናገለግለው የሚዋጋን

ሰይጣን ዲያብሎስን አጥብቀን ልንቃወመው ያስፈልጋል ።

6 . የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በደጅ እንደሆነ አውቀን በቅድስናና በጽድቅ

እየኖርን ህወታችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንድናዘጋጅ ያስፈልጋል ።

7 . ያለንበት ዘመን ሐጢያት የበዛበት ዘመን ስለሆነ ለቅድስናችን ታጥቀን ቆርጠን

በህወታችንን ኢየሱስን አክብረን በምድር ላይ አስከብረን ሐጢያትን እንቢ ብለን

ወንጌልን ሰብከን መሞትም ካለብን ለወንጌል ተሰውተን ማለፍ ይኖርብናል ;;

# ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን

**2004 Nw 63rd st**
**Seattle, Wa 98107**

**206 793 8186**

*Full gospel church*



*እግ\ርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ ፡ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ ፡ ይሮጣሉ ፡ አይታክቱም ፡ ይሄዳሉ ፡ አይደክሙም ።*

*ኢሳ 40 - 31*

**በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር**
**አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ። ዮሐንስ ወንጌል 3 -16**

## <u>የቤተክርስቲያኒቱ ራእይ</u>

1. ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ መስበክ የመጀመርያ ተልእኮአችን ነው። በማርቆስ ወንጌል እንደ ተጻፈው ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ ወደ አለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። የማርቆስ ወንጌል 15፡16

2. ቅዱሳን በእግ\ር ቃልና በጸሎት እንዲበረቱ ማስተማርና ማስታጠቅ እንዲሁም ለአገልግሎት ማብቃት። ልጆቼ ሆይ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ አገልጋዮቹም ትሆኑ ዘንድ ታጥኑለትም ዘንድ እግ\ር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ። መጽሃፈ ዜና መዋዕል ካልእ 29፡11

3. በተለያዩ ችግሮች የሚያልፉትን በያሉበት በመገኘት መጸለይ። በዚያች ሰዓት ከደዌና ከስቃይ ከክፉዎች መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ፡ ለብዙ ዕውሮችም ማየትን ሰጠ ። የሉቃስ ወንጌል 7-21

4. መተለያዩ ምክንያት የተጎዱ ራእያቸውን የጣሉ እንደገና እንዲነሱና እንዲበረቱ በምክርና በጸሎት መርዳት።

ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግ\ርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ።
2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡6

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
አብራሃም ይስሃቅ



## <u>የቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት</u>

**እሁድ የአምልኮ ጊዜ**
ከ 3 ፡ 30 ፒ.ኤ.ም  እስከ 6፡00

**እሁድ ጸሎት**
ከ 2 ፡ 30 እስከ 3 ፡ 30

**ሃሙስ ጸሎት**
ከ 6፡00 ፒ.ኤ.ም እስከ 8፡00

**አርብ ጸሎት**
ከ 6፡00 ፒ.ኤ.ም እስከ 8፡00

**ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ።**